# መቋጫ የሌለው  የፖለቲካ ግልሙትና ለኘሬስ ነፃነት ምኑ ነው?

**ከአብርሃም ዘ-ደብረ ብርሃን**

aberhamisme@gmail.com

***ገለልተኛ የሀሳብ ክፍል***

***ባልዳበረበት ስብዕና እና ቡድን***

***ውስጥ ነጻ ጋዜጠኝነት እና ነጻ ፕሬስ***

***ብሎ ነገር አይታሰብም***

ሰዎቹ ምን ነካቸው? እንደ መርዶ ነጋሪ፣ እንደ ሙሾ ደርዳሪ "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" ፣ የጥንቆላ ንግርት፣ የሀሣዊ ነብይ መዓት መጣ ጨለምተኛ ትንቢት፣ ወዬ ይህች አገር ልትጠፋ ነው… ወዬ ይኸ ሕዝብ የመጨረሻው ዘመን ላይ ደርሷል፡፡ ወዬ ከሠማይ እሳት ወርዳ ሕዝብን ታቃጥላለች….. ወዬ ምድር ተከፍታ መንግሥትን ትውጣለች ….ወዬ በቤተ መንግሥት የሚያድሩ የሰማይ ስባሪ የሚያክል ኮከብ በላያቸው ላይ ይወድቃል፡፡ ወዬ…… ተስፋ ለሌላቸው ተስፋ የሚሆን አይገኝም….. ድምፄን የምትሠሙ ሁሉ ማቅ ለብሳችሁ… ትቢያም በላያችሁ ላይ ነስንሳችሁ በአመድም ላይ ወድቃችሁ ትማፀኑ ዘንድ ትዕዛዜ ይህች ናት የሚሉ ሚዲያዎችን ምን እንበላቸው?

እልፍኛችሁን ዘግታችሁ የተመካከራችሁትን እሠማለሁ፡፡ ታደርጉት ዘንድ ያሳባችሁትንና የተለማችሁትን አውቃለሁ፡፡ እናንተ ከምትሉት ይልቅ ያላችሁትን እነግራችሁ ዘንድ መናፍስተ ዕውቀትን ገልፀውልኛል፡፡ ታደርጉት ዘንድ የፈቀዳችሁትን እናንተ ለሕዝብ ከመግለፃችሁ በፊት እገልፀው ዘንድ ስልጣንን ከሰማይ ተቀበልኩኝ…. ድምፄን ባትሠሙ አለም አይሠማችሁም፡፡ የምነግራችሁን ባትቀበሉ ቁጣየ ይከብድባችኋል፡፡ ቃል ለምድር ለሠማይ ሟርቴ በላያችሁ ላይ ይፈስስ ዘንድ መንፈሴ ነገረኝ የሚሉንን፣ ቃዥተው ሊያቃዡን የሚሞክሩትን "ጋዜጠኞች" ወይም የሚዲያ ጠበቆች ነን የሚሉንን ምን እንበላቸው?

በሀሣብ ቅዠት ውስጥ ተጠላልፈው የወደቁ፣ የግልሙትና ረከቦት ዘርግተው ጨለምተኛ ስኒዎቻቸውን እየዘቀዘቁ የፖለቲካ ጥንቆልናቸውን በሟርተኛ ሚዲያዎቻቸው የሚያስተጋቡ እነዚህ ጋዜጠኛ ነን ባዬች ከሚዲያ ነፃነት ጋር ያላቸው ዝምድና ምንድን ነው? ሀሣብን በነፃነት የመግለጽ መብት /freedom of expression/ በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ ለሕዝብና ለአንዲት ሉአላዊት ሀገር ደህንነት ስጋት በማይፈጥር መልኩ ተግባር ላይ መዋል እንዳለበት የማይስማማ ካለ ጥፋትንና ርስ በርስ መተላለቅን ማዕከል አድርገው የተቋቋሙ ጨለምተኛ ጋዜጠኞችና እነ ኢሳትን የመሳሰሉ ሙሾ ደርዳሪ ሚዲያዎች ካልሆኑ

በስተቀር ሁሉም ይስማማል፡፡ የሚዲያ ነፃነት ከፕሬስ ነፃነት፣ የፕሬስ ነፃነት በጥብቅ ፕሮፌሽናል ዲሲፕሊን ከሚመራ የጋዜጠኝነት ሙያዊ ነፃነት ጋር በጥብቅ የሚተሣሠርና አንዱ ከአንዱ ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡

ሀሣብን በነፃነት የመግለጽ መብትን ተጠቅሞ የሚርት ነጋሪት መጐሰምን ከየትኛው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ እንደተቀዳ ግልጽ ባይሆንም ለሚርተኛ ሚዲያዎችና "ነፃ ጋዜጠኞች ነን" ባዬች ለጥፋት ህልማቸውና ለሚርት ቅዠታቸው የሕግና የሕዝብ ጥቅም ጉዳይ ጉዳያቸው ስላልሆነ በሙት መንፈስ የጉሪ ቅኝት "ታልቃላችሁ" የጥፋት በገናቸውን ይደርድሩብናል፡፡ ለጥፋት በገና ድርደራቸው አድማቂና አሟሟቂ የሆኑት የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነን ባይ ድርጅቶችና ግለሠቦች ገፀ በረከት ቢያጅባቸው የልብ ልብ እየተሠማቸው አንድ አንዴ የአራት ኪሎ ቤተመንግሥት አቃቢ መንበር ሲሆኑ አንድ አንዴ ደግሞ ራሳቸውን የጦር ኃይሎች ኢታማገር ሹም አድርገው የተለመደ "አውቅላችኋለሁ" የጥፋት እምቢልታቸውን ይነፋብናል፡፡

በሕግ አምላክ እንዳንላቸው የእነሱ ነገር የሕግ ጉዳይ አይገባቸውም፡፡ሚዛናዊ የመልካም ጠባይ እሴታቸው የወረደ ስለሆነም የሉአላዊት ኢትዬጲያንና ኢዬጵያውያንን ጥቅምና ደህንነት አንስተን ልንሞግታቸው አንችልም፡፡ትክክል የሆነውን ሳይሆን ትክክል ነው ብለው ያመኑበትን ብቻ በማራመድ የሚታትሩ፣ ከጸረ ሰላም ኃይሎች እና ከሽብር አቀንቃኞች ጋር የተወዳጁ፣የኢትዮÉያ ህዳሴ ብሎ ነገር የማይገባቸው፣የኢትዮÉያ እድገት የሚቆጠቁጣቸው እና እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አይነት የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ ከሚያራምዱ ጸረ ኢትዮÉያ አቋም ካላቸው አገሮች እና ቡድኖች ጋር ተሰልፈው የኢትዮÉያ ትውደም መዝሙር እያስተጋቡ ለጥፋታችን የሚዋትቱ ናቸው እና መግባባት አንችልም፡፡ ብቻ እንደለመዱት በባእድ አገር ከባዕድ ምድር በቃረሙት አጉራዘለል ዘመናዊነት ከአባቶቻችን ያልወረስነውን እንድንወርስ ሊያስገድዱን፣ የማናምንበትን ሊጭኑብን ለማንም ነጭ ደላላ እጅ ስጡ ይሉናል፡፡ በኒዬ ሊበራል የገበያ አክራሪነት ቅኝት እጃችንን ጠምዝዘው ላመኑበት መናፍስታዊ ሙሾ ጭዳ ሊያደርጉን ይዳዳሉ፡፡

ነፃ ሚዲያ እና ነፃ ጋዜጠኞች ነፃ አገር፣ ነፃ ሕዝብና ነፃ ህሊና የመፍጠር አቅማቸው ብርቱ ነው፡፡ ይህንን አቅም ለመፍጠር በሙያ ነፃነት ውስጥ ለሙያ ክብር ተገዥ መሆን፣ ሙያው ለሚፈልገው ጥብቅ ሥነ-ምግባርና የአሠራር መርሆ ታማኝ መሆንን ይጠይቃል፡፡ ሀሣብን በነፃነት የመግለጽ መርሆ በሀሣቡ ትክክለኛነትና ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ላይ ያተኮረ፣ ለአንድ አገር ሕዝብ ደህንነት ተገቢውን ትኩረትና ጥንቃቄ የሚወስድ፣ በሕግና በመልካም ጠባይ የሚመራ ካልሆነ ነፃ ሚዲያ ብሎ ነገር አይኖርም፡፡ ነፃ ጋዜጠኞችም ለተከበረው የጋዜጠኝነት ሙያ ዕሴት ተገዥ ካልሆኑ ነፃነታቸውን በነፃ ፈቃዳቸው ደፍቀዋልና "ነፃ ጋዜጠኞች" ሊሆኑ ከቶውንም አይችሉም፡፡

ነፃ ፕሬስ ለሀሣብ ነፃነት ልጁ እንጅ አባቱ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ያለ ነፃ ፕሬስ ነፃ ሀሣብ መኖር ሲችል ነፃ ሀሣብ በሌለበት ግን ነፃ ፕሬስ ሊኖር አይችልም፡፡ ነፃ ፕሬስ ነፃነቱን ማረጋገጥ የሚችለው ለነፃ ሀሣብ በሚሠጠው ዋጋ ልክ ነው፡፡ ነፃነቱ በተገፈፈ የሀሣብ ድብብቆሽ ውስጥ ስለ ነፃ ፕሬስ መወትወትም ሆነ መሟገት ነፃነት በተነፈገው ሀሣብ ውስጥ ነፃነትን ለመፍጠር ከሚደረግ የፖለቲካ ግልሙትና የዘለለ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ከአንደኛው ኮርነር ሌላኛው ኮርነር እየተለጋ፣ ሲሻው የጥፋት ነጋሪት

ሲጐስም አልፎ አልፎ ራሱን በነብይ አምሳል አቁሞ በመናፍስታዊ መነጽር ያግበሰበሰውን ቧልት በቅዠት ብዕሩ አለምን ሲያደናግር በሚውል የሀሣብ ጡዘት ውስጥ ነፃ ሀሣብና ነፃ ኘሬስ መቃብራቸውን አግኝተው ካልሆነ በስተቀር ለልዕልናቸው መሠረት የሚሆን እድል ፈንታ የላቸውም፡፡

ነፃ ኘሬስ ያለ ነፃ ሀሣብ፣ ነፃ ሀሣብ ያለ ነፃ ኘሬስ ባዶ ብርጭቆን ወደ ጉሮሮ ለግቶ ከውሃ ጥም ለመርካት የሚደረግ መቅበዝበዝ ነው፡፡ ቀድሞውንም ነፃ ያልሆኑ " ጋዜጠኛ " ነን ባዬች በተኮለኮሉበት የነፃ ሀሣብ ማዕድ ነፃ ዳቦ መቁረስ የሚታሠብ አይሆንም፡፡ መልካም ባለሙያ የጋገረውን ዳቦ እንጀራ ነው እያሉ ማብጠልጠል፣ ያልተጨመረበትን ቅመም ተጨመሮበታል በሚል ተራ ሙግት የዳቦውን ጋጋሪና ተመጋቢ ማደንቆር የነፃ "ጋዜጠኛ" ነን ባዬች አስማታዊ ቅዠት ነው፡፡

አነዚህ " ነጻ ጋዜጠኛ " ነን ባዬች በተስፋይቱ ምድር ኢትዬጵያ እየተከናወነ ያለው ተአምራዊ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሽግግር ቢያስደምማቸው ያላሠቡት እየሆነ መምጣቱ የመላምታቸውን ፍሬ ከርስኪነት ስላጋለጠባቸው ከጋዜጠኝነት ሙያዊ ሥነ-ምግባር ያፈነገጠ አድማሣዊ ቅዠት ውስጥ ስለከተታቸው በሙት መንፈስ ክታባቸውና በዝርው-ቃል ድስኩራቸው የተስፋይቱን ምድር ሕዝቦች ለማወናበድና ዘወትር ለሚመኙት የርስ በርስ  መተላለቅ ህልማቸው ራሳቸውን አሣልፈው ለሠጡት የኒዬ ሊበራል አምልኮ ሥርዓታቸው አገራችንን መስዋዕት ሊያደርጉ የጭካኔ ሰይፋቸውን ይመዛሉ፡፡ በነፃ ኘሬስና በነፃ ጋዜጠኝነት ስም ለሚፈጽሙት አይን ያወጣ ወንጀል ተጠያቂ መሆን አለባቸው ሲባል የቤተ አምልኳቸው ታቦታት የሆኑት የሰብአዊ መብት ታጋይ ነን ባዬች እነ አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዩማን ራይትስ ዎች የግልሙትና መቋሚያቸውን እየዘቀዘቁ አገራችንን ይረግማሉ፡፡ ህዳሴያችን ያጥላላሉ፡፡

እነዚህ የሰብአዊ መብት ትርጉም የጠፋባቸው የሰብአዊ መብት ታጋይ ነን ባይ ድርጅቶች ጫጩቶቿን በክንፎቿ አቅፋ ሙቀት የምትለግሰዋን ዶሮ ከጫጩቶቿ ነጥለው መስዋዕት በማድረግ ግለ ልዕልናቸውን በየዋህን ሥነ-ልቦና ውስጥ ለማስረጽ ሁሉንም ሰይጣናዊ አማራጭ ይከተላሉ፡፡የሰማኒያ ሚሊየን ሕዝብ መኖሪያ የሆነች አገራችን በጀመረችው የህዳሴ ጉዞ ከራሷ አልፋ ለጐረቤት አገሮች መመኪያና ዋስትና እየሆነች መምጣቷን እያወቁ የአንዲት ድሀ አገር ወደተሻለ ደረጃ መምጣት ሊያስደስታቸው ሲገባ ከአፈርኩ አይመልሰኝ በትራቸውን በሠበብ አስባብ ሲያወናጭፉት ማየት የተለመደ ከመሆን አልፎ መገለጫ ባህላቸው አድርገውታል፡፡

የሰብአዊ መብት አያያዝን እነሱ ከሚያራምዱት ርዕዬታዊ  ፈለግ አለመጣጣም ጋር እየቀላቀሉ ድብቅ የሁለት ምላስ አጀንዳቸውን በነፃይቱ ምድር ኢትዬጵያ ላይ ለመጫን ያልተሳካላቸው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነን ባይ ድርጅቶችና " የነፃ ኘሬስ " አቀንቃኝ "ነፃ ጋዜጠኞች" የጀመርነውን የህዳሴ ጉዞ ለማሠናከል የሚጫወቱትን የጥፋት ካርታ እየመዘዙ እንደ ሜትርዬሎጂ ሳይንሳዊ ትንታኔ ጥንቆላ አይሉት ትንበያ ፖለቲካዊ ቅዠታቸውን ድንገት ብንን እንዳሉ ያስተጋቡታል፡፡

እነዚህ አካላት ባላቸው የአላማ ትስስር ሳይግባቡ ተግባብተው የአጥፍቶ  ጠፊ ቅኝታቸውን እያዜሙ በተሻለ ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ እምርታ ላይ የምትገኘዋን የተስፋይቱ ምድር እናት አገራችንን ከሁለት አሥርተ አመታት በፊት ወደ ነበረችበት ማለፊያ የሌለው አዘቅት ተመልሳ እንድትዘፈቅ በሰብአዊ መብት

ስም የማባበያ ግልሙትናቸውን ይቆምሩባታል፡፡ በውጭ የሚኖሩ አኩራፊ ተቃዋሚዎች እነ ግንቦት 7 ጨምሮ በነፃ ፕሬስና በነፃ ጋዜጠኝነት ስም እየነገዱ በአለም ባንክ አለም አቀፍ የዕድገት መመዘኛዎች የተሻለ እምርታ ያስመዘገበችውን አገር መርጦ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለወለድ የ1.15 ቢሊየን ዶላር ብድር ተጠቃሚ እንድትሆን ሲወስን መርዝ እንደወሰደ ውሻ ቁጣ አይሉት ብስጭት ጭራቸውን መቁላት ጀምረዋል፡፡

እኛን ደስ ብሎናል፡፡ ምክንያቱም አለም የሚደሰትባት እና ዕምነት የሚጥልባት አገር ባለቤቶች በመሆናችን ደስታችን እጥፍ ድርብ ነው፡፡ ይች አገር ታድጋለች፡፡ ይች አገር በሕዝቧና በልማታዊ መንግሥቷ ጥረት የገባችበትን እልህ አስጨራሽ የለውጥ ትግል ያለምንም ጥርጥር ታሳካለች፡፡ ይች አገር በግለሠብና በቡድን መብት መከበር ጽኑ አለት ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የዘረጋችና ይህንንም ለአለም ያሣየች አገር ናት፡፡ ይች አገር ብዝሃነት የሰፈነባት፣ የራስን እድል በራስ በመወሠን መብት የምታምን፣ የብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦችና የኃይማኖት እኩልነት የሠፈነባት የምሥራቅ አፍሪካዋ ንግስት ናት፡፡ ንግስናዋ በንጉሰ ነገስት የትምክህት አጥር የተሸበበ አይደለም፡፡ በኪራይ ሰብሳቢነት ቅብብሎሽ የተገነባ፣ ጠባብነትና ጥቅመኝነት የወለደው፣ ከሕዝብ ፍላጐት በተቃርኖ የቆመ ልዕልና አይደለም፡፡ ንግስናዋ በአብሮነት ላይ የተመሠረተ የጐረቤት አገሮች ማደግ፣ መበልፀግና በሠላም መኖር ለእኔ ዕድገትና ብልጽግና፣ የህዳሴ ቀጣይነት ዋስትና ነው በሚል ዲሞክራሲያዊ እና ልማታዊ አለት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እናንተ ክፉት በልቡናችሁ ተርፎ በአንደበታችሁ የሚፈስ፣ በብእራችሁ የሚንገፍቀገፍቅ የጥፋት መልዕክተኞች መልዕክቴን ትሰሙ በልቡናችሁም ታሣድሩት ዘንድ ይህችን ጦማር ላክሁላችሁ፡፡ በላያችሁ ረበው የሚያስጨንቋችሁ፣ ከህቅ ይልቅ " ለበሬ ወለደ" የአምልኮት ሥርዓታችሁ ኢትዮጵያን ጣልልን ኢህአዴግን አጥፋልን ስትሉ የምትሠውት ነፃ ፕሬስ፣ ነፃ የጋዜጠኝነት ሙያና የሰብአዊ መብት ተሟጋችነት እንዳይፋረዳችሁ ለህሊናችሁ እና ለሙያችሁ ሱባኤ ግቡ፡፡ ሁሉን መርምሩ መለካሙን ያዙ!

**የተስፋይቱ ምድር የምሥራቅ አፍሪካዋ ኢትዮጵያ ይቅር ትበላችሁ!**